በኅብረቱ እምነት የሁሉም ርብርቦሽና የትግሉ ንጥጥር የሥርዓት ለውጥ ማስገኘትና ማምጣት ላይ መሆን ይኖርበታል:: የተቋቋመበት መንፈስም ይኸው ነው:: የኅብረቱ የትግል ትኩረት መሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት እንጂ አገዛዙ የተሻለ ሕጋዊነትን ያገኝ ዘንድ አጃቢ ለመሆን ወይም ፓርላማ ውስጥ አንጻራዊ የሆነ በርከት ያለ መቀመጫ በማግኘት የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅሞችና የዜጎቿን መብቶች የሚያስጠብቅ ለውጥ ማምጣት ይቻላል በሚል ብዥታ ወይም ቀቢፀ-ተስፋ አይደለም::

ኅብረቱ የሚከተለው የሰላማዊ ትግል አካል የሆነው ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ እውን እንዲሆን የሚቻለውን ሁሉ ከማድረግ አኳያ አገዛዙ በየጊዜው የሚወስዳቸውን ቀጣይ ፀረ-ሕዝብና አፍራሽ ተግባራቱን በመቃወም በአገር ውስጥም ሆነ በውጭው ዓለም ኢትዮጵያውያንን የማስተባበር ሥራውን ቀጥሏል:: አገዛዙ ቀደም ሲል በጋምቤላ ወገኖቻችን ላይ ያደረሰውን የዘር ማጥፋት እርምጃ፥ በነፃው ፕሬስና በሙያ ማኅበራት ላይ የሚወሰደውን አፋኝ ድርጊቶች፥ በቅርቡም በኢሕአዴግ ጠቅላይ ሚኒስትር የተወሰደውን የሰላም ነጥብ ተብዬ ጉዳይ ወዘተ... በመቃወም ሰላማዊ ሰልፎችና ልዩ ልዩ ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴዎችን አድርጓል፤ ያለማቋረጥም ይቀጥልበታል:: አሁንም ኢትዮጵያውያን ልብ ሊሉት የሚገባው ጉዳይ አገዛዙ በሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ እነዚህ ፀረ-ሕዝብና ሃላፊነት የጎደላቸው ደንታ ቢስ እርምጃዎች በጭራሽ እንደማይቆሙ ነው:: በመሆኑም የአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ በየጊዜው ለሚያደርጋቸው ቀጣይ አፍራሽ እርምጃዎች ተቃውሞአችንንና ንዴታችንን በፈለገው ብዛትና መጠን መግለጹ በቂ አለመሆን ብቻ ሳይሆን አቅጣጫ የሳተና በጣሙን የተዛባ ነው የሚሆነው:: መልሱ አንድና አንድ ብቻ ነው:: ማንኛውም ሃላፊነት የሚሰማው የፖለቲካ ድርጅት ከሲቪክና የሙያ ማኅበራት ጋር በመሆን በተጣመረና በተጠናከረ ትግል አገዛዙን ከሥልጣን ማስወገድ ብቻ ነው ቁልፉ:: ለዚህ ኅብረቱ ዛሬም የጋራ ትግል ጥሪውን ያቀርባል:: የሕዝቡንም ትብብር በአጽንዖት ይጠይቃል::

# የዜና አምድ

## ኢዴኃኅ መጭውን ምርጫ እንደ ትግል ስልት እንጂ እንደ መጨረሻ ግቡ አይመለከተውም ተባለ

ኢዴኃኅ በኢሕአዴግ ሥርዓት ሥር ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ ማካሄድ የማይቻል መሆኑን ቢገነዘብም የነፃና ፍትሓዊ ምርጫ ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሟሉና እንዲስተካከሉ በመታገል ኢሕአዴግን ለማስገደድና ለማጋለጥ ብሎም ሕዝቡን በማቀፍና የትግሉ አጋር በማድረግ የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት እንደሚቻል እምነቱ መሆኑን በቅርቡ ከዜና ኢዴኃኅ ዘጋቢዎች ጋር የአመራር አባላቱ ካደረጉት ሰፊ ቃለ ምልልስ ለማወቅ ተችሏል።

የአመራር አባላቱ በኢሕአዴግ መንግሥት ውስጥ መድበለ ፓርቲና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊኖርም ሊዳብርም ስለማይችል ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በሰላማዊ የትግል ስልት ሥርዓቱንና ሕገ-መንግሥቱን ለማስወገድና ለመሻር ብሎም የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሕገ-መንግሥት ለማርቀቅና በህዝብ ለማጸደቅ በጋራ መቆም እንዲሁም የሥርዓቱን እውነተኛ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ገበናና አምባገነንነቱን አራቁቶ ለማሳጣት መጣር ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

የኢዴኃኅ የአመራር አባላት ጨምረው ሲያብራሩም ፀረ-ዴሞክራሲያዊ በሆነ ሥርዓት ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ውድድር የሕዝብ መብትና ምርጫ ይከበራል ወይም እውን ይሆናል ብሎ ማሰብ ከነባራዊ ሁኔታ ጋር የተጣላ ቀዠት ነው። እንዲያው በደፈና በምርጫ ተሳትፎ ወይም የፓርላማ ወንበር አጠራቅሚ ኢሕአዴግን እተካለሁ የሚል ፍላጎት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያመጣው አንዳችም ፋይዳ ስለሌለው በምርጫ መሳተፍ ብቻ ለኅብረቱ የመጨረሻ ግቡ ሊሆን አይችልም።

ይልቁንም ወደ መጨረሻ ግቡ ሊያደርሰው የሚችል አንዱ የትግል ዘዴና ስልት እንደ ብለዋል፡፡

የዜና ኢ.ደ.ኃ.ኅ ዘጋቢዎች ከኢ.ደ.ኃ.ኅ የአመራር አባላት ጋር ያደረጓቸው እጅግ ሰፊ ቃለመጠይቆች ከጃንዋሪ 22 2005 ጀምሮ በተለያዩ አገሮች በሚገኙ የመገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉ መሆኑንም ለማወቅ ተችሏል፡፡

## በኢትዮጵያ ደሞክራሲያዊ ኃይሎች አስተባባሪነት በኢትዮጵያ ዋና ዋና ከተሞች የሚደረጉ ሕዝባዊ ስብሰባዎች እንደቀጠሉ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ደሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት በአገር ቤት በተለያዩ ከተሞች የሚያደርጋቸው ሕዝባዊ ስብሰባዎች አሁንም በሰፊው እንደቀጠሉ ነው፡፡

ግንቦት 22 ቀን 1996 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ መስቀል አደባባይ ከመቶ ሺህ በላይ የተገመተ ህዝብ የተገኘበት ህዝባዊ ስብሰባ በተሳካ ሁኔታ ከተጠናቀቀ ጀምሮ በሌሎችም የአገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች የሚደረጉ ሕዝባዊ ስብሰባዎች በአመርቂ ሁኔታ እየተካሄዱ መሆኑን ከአገር ቤት የዜና ኢ.ደ.ኃ.ኅ ቃል አቀባዮች ካስተላለፏቸው ዘገባዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

ሐምሌ 4 ቀን በአዋሳ ከተማ ከሁለት ሺህ የማያንስ ሕዝብ የተገኘበት ስብሰባም እንደ አዲሳባው ሁሉ የተሳካ መሆኑ ቀደም ሲል በልዩ ልዩ መገናኛ ብዙኃን የተዘገበ እንደነበር የሚታወስ ሲሆን በቦታው የተገኙት የኢ.ደ.ኃ.ኅ የአመራር አባላትም ስለኢትዮጵያ ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታና ስለኅብረቱ መሰረታዊ ዓላማዎች መግለጫ የሰጡበት፥ ስለ ነፃና ፍትሓዊ ምርጫም ማብራሪያ የተደረገበት እንደነበር በዜና ኅብረት ቁጥር ሁለት መዘገቡ ይታወሳል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ጥረቱ ቀጥሎ በጅማ ከተማ ታኅሣስ 10 ቀን 1997 ዓ/ም የተደረገው ሕዝባዊ ስብሰባም የተሳካ እንደነበር የታወቀ ሲሆን በኢ.ደ.ኃ.ኅ ሊቀ-መንበር በዶ/ር መረራ ጉዲና የተመራው የኅብረቱ ከፍተኛ የልኡክ ቡድን ስለመጪው ምርጫና አስቀድሞ መደረግ ስለሚገባቸው ቀድመ ሁኔታዎች እንዲሁም በአገዛዙ መሪ በአቶ መለስ ዜናዊ በቅርቡ ስለተወሰደው የተዛባ የሰላም ሃሳብ ተብዬ አቋም ኅብረቱ ያለውን ተቃውሞ ለሕዝቡ ግንዛቤ ያስጨበጠበት መሆኑ ተዘግቧል፡፡

ቀጥሎም በባሕር ዳር ከተማ በታሕሣስ 17 ቀን 1997 ዓ/ም በተደረገው እጅግ ደማቅ ሕዝባዊ ስብሰባ በኅብረቱ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀ-መንበር በዶ/ር በየነ ጴጥሮስ የተመራው ከፍተኛ የልኡክ ቡድን ተገኝቶ ስለ ኢ.ደ.ኃ.ኅ ዓላማና ግቦች፥ ስለነፃና ፍትሓዊ ምርጫ፥ ስለአዲሱ የሰላም ሃሳብ ተብዬ ጉዳይ፥ ወዘተ... ከተሰብሳቢው ህዝብ ጋር ሰፋ ያለ ውይይት አድርጓል፡፡ ሕዝቡም ቀደም ሲል በአዋሳና በጅማ እንደታየው ሁሉ በአገዛዙ ላይ ያለውን ምሬትና መንገፍገፍ በግልጽ ያስተጋባበት፥ ኅብረቱ በአካባቢው ጽሕፈት ቤቱን በአስቸኳይ እንዲከፍትና ትግሉን እንዲመራ የጠየቀበት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከባሕር ዳር ቀጥሎ ኢ.ደ.ኃ.ኅ በደሴ የጠራውም ስብሰባ እጅግ ባማረና በደመቀ ሁኔታ የተከናወነ ሲሆን ዶ/ር መረራ ጉዲና ከፍተኛውን የልኡክ ቡድን እንደመሩ ታውቋል፡፡
የልኡክ ቡድኑም ለተሰብሳቢው ሕዝብ ስለ ኢ.ደ.ኃ.ኅ ዓላማና ግብ ስለ ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ ኅብረቱ በአቶ መለስ የሰላም ሃሳብ ተብዬ ላይ ያለውን ግልጽ አቋም በሰፊው ያብራራበት ሲሆን የሕዝቡ የጋለ ተሳትፎ እጅግ የሚያኮራና አበረታች እንደነበር የኢ.ደ.ኃ.ኅ ዘጋቢ ገልጿል፡፡ ቀደም ሲል ተመሳሳይ ስብሰባዎች በተደረጉባቸው ቦታዎች እንደተጠየቀው ሁሉ የደሴ ሕዝብም ኅብረቱ በአካባቢው ጽ/ቤቱን በአስቸኳይ እንዲከፍትና አመራር እንዲሰጥ ጥያቄ ያቀረበበትና ኅብረቱም ለጥያቄው ምላሽ ለመስጠት ቃል የገባበት መሆኑ ተገልጿል፡፡
በጅማ፥ በባሕር ዳርና በደሴ ከተሞች በተካሄዱት ሕዝባዊ ስብሰባዎች ኅብረቱን በቅርቡ የተቀላቀለው የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት ከፍተኛ ተሳትፎ እንዳደረገ በተጨማሪ ተዘግቧል፡፡

ከዚሁ ጋር ቀጣዮቹ የኢ.ደ.ኃ.ኅ ሕዝባዊ ስብሰባዎች በመቀሌና በሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች እንዲሆኑ እቅድ

መያዙንም የዜና ኢ.ደኃኅ ዘጋቢዎች ከአገር ቤት ካስተላለፉት ዜና ለማረጋገጥ ተችሏል።

## በልዩ ልዩ የዓለም ከተሞች በኢ.ደኃኅና በደጋፊዎቹ አስተባባሪነት ጉባኤዎች እየተዘጋጁ መሆኑ ታወቀ።

የኢትዮጵያ ደሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት ስለመጪው ምርጫ ያለውን ግልጽ አቋም ይበልጥ የሚያብራሩ ከምርጫው በሁዋላ ስለሚቋቋመው የመንግሥት ዓይነትና መቀረጽ ስለሚኖርበት የሕገ-መንግስት ዓይነት የሚያስረዱ እንዲሁም ስለ አገራችን የድንበር መከበር ጥያቄና ሌሎችም ወቀታዊ ጉዳዮች የሚያወያዩ ጉባዔዎች በሰሜን አሜሪካ በአውሮጳ በእስያና በአውስትራሊያ ዋና ዋና ከተሞች እየተዘጋጁ መሆናቸውን ከየዓለማቱ የድጋፍ ኮሚቴዎችና የኢ.ደኃኅ ወዳጆች የሚደርሱት ዘገባዎች ጠቆሙ።

በቀርቡ ሊደረጉና ዝግጅታቸው በመጠናቀቅ ላይ በሚገኙ በነዚህ ኮንፍረንሶችም ላይ ከኢትዮጵያ የሲቪልና የሙያ ማህበራት መሪዎች የሚገኙበት ሁኔታ እየተመቻቸ መሆኑ ጨምሮ የተገለጸ ሲሆን በነዚህ ዝግጅቶች ላይ የኢትዮጵያውያን ተሳትፎ ፍጹም ወሳኝነት እንዳለውም ተጠቁሟል ።

ዝግጅታቸው በበቂ ሁኔታ ከተጠናቀቁት ውስጥ በሎስ አንጀለስ የኢ.ደኃኅ የድጋፍ ኮሚቴ አስተባባሪነት በማርች 5 2005 እ. አ. አ. ሊደረግ የታቀደው ስብሰባ በዓይነተኛነቱ የሚጠቀስ ሲሆን በዝግጅቱ ላይ ዶክተር ታዬ ወልደ ሰማያት የአንጋፋው የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር ፕሬዚደንት እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል።

ተመሳሳይ ጉባኤ በዋሽንግተን ዲሲ ለፌብሪዋሪ 2005 መጨረሻ የተጠራ ሲሆን የኢ.ደኃኅና የሌሎችም ድርጅቶች የአመራር አባላት እንዲሁም እውቀ ምሁራን በጥናትና በምርምር የተደገፉ በልዩ ልዩ ወቀታዊ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ሥራዎች እንዲያቀርቡ ግብዣ የተደረገ መሆኑን ከጉባዔው አዘጋጆች ለማወቀ የተቻለ ሲሆን ዝርዝር መግለጫ በቀርቡ ለሕዝብ ይፋ እንደሚሆንም ተጠቀሷል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በአውሮጳም የኢ.ደኃኅ ደጋፊዎችና ወዳጆች ተሳትፎን ያካተተ በኢ.ደኃኅ አስተባባሪነት የተዘጋጀ ጉባኤ ለጃንዋሪ 23 2005 እ. አ. አ. መጠራቱ የታወቀ ሲሆን በጉባዔው የጥናት ጽሁፍ አቅራቢ ምሁራንና የአዳራሽ ዝግጅቱ የተጠናቀቀ መሆኑን ከአውሮጳ የኢ.ደኃኅ ቢሮ የተገኘው መረጃ አመልክቷል።

የእስያና የአውስትራሊያ የኢ.ደኃኅ የድጋፍ ኮሚቴዎች በቀርቡ ዝርዝር ፕሮግራማቸውን እንደሚያሳውቁ ለተግባራዊነቱም የአካባቢው የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ አባላት ተሳትፎ የጎላ መሆኑንም የደረሱን ዘገባዎች ጨምረው አመልክተዋል።

## ለኢ.ደኃኅ ተግባራት ማከናወኛ ተጠያቂነትና ሃላፊነትን ያካተተ የገንዘብ ማሰባሰብ በስፋት እየተካሄደ መሆኑ ተገለጸ።

የሰሜን አሜሪካ የኢ.ደዛህ የድጋፍ ኮሚቴዎች በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሃገር ኢ.ደዛህ መሰረቱን ለማስፋት እንዲያስችለውና በመጪው ምርጫም ጉልህ ሚና እንዲጫወት በቁሳቁስና በገንዘብ የሚታገዝበትን መንገድ በበለጠ ለማጠናከር በከፍተኛ እንቅስቃሴ ላይ መሆናቸው ታወቀ።

የድጋፍ ኮሚቴዎቹ በጃንዋሪ 16, 2005 እ. አ. አ. ባደረጉት ስብሰባ ከሰላሳ ሶስት በላይ ከልዩ ልዩ የሰሜን አሜሪካ ከተሞች የተወከሉ አባላት የተገኙ ሲሆን በተለይ የኢ.ደኃኅን የገንዘብ አቅም በማዳበር በኩል ፈጣን እርምጃ ለመውሰድ ስምምነት ላይ ከመድረሳቸውም በላይ ይኸንንም የገቡትን ቃል እስከ ፌብሪዋሪ 2005 እ. አ. አ. መጨረሻ ሊያጠናቅቁና ለኢ.ደኃኅ የፋይናንስ ኮሚቴ ሊያስረክቡ መስማማታቸውን በቴሌ ኮንፍረንስ ስብሰባው ላይ ከተገኘው የዜና ኢ.ደኃኅ ዘጋቢ ለማወቅ ተችሏል።

በስብሰባው ላይ የጉዳዩን አጣዳፊነት የተረዱት የቤይ ኤርያ፥ የዳላስ፥ የሲያትል፥ የሚኒሶታና የቶሮንቶ የድጋፍ ኮሚቴዎች ሊያዋጡ ቃል የገቡትን የገንዘብ መዋጮ ያስረከቡ ሲሆን ሌሎች ልዩ ልዩ የገንዘብ ማግኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ግዴታቸውን በቀጣይነት ለመወጣት ቃል መግባታቸውን ለማወቅ ተችሏል።

በሌላ በኩል በስብሰባው ላይ የተገኙት የኢዴሃህ የፋይናንስ ኮሚቴ ተወካይ ለመጪው አጭርና ከባድ የኢዴኃኅ የፈተና ወቀቶች የአዲሳባውን ጽሕፈት ቤት ለማጠናከር፥ የአካባቢ ጽሕፈት ቤቶችን ለመክፈት፥ ለሰራተኞች ደምወዝ፥ በየምርጫ ጣቢያው ሕዝቡን ለመድረስና ለምርጫው ለማዘጋጀት እንዲሁም ለመገናኛ ብዙኅን መጠቀሚያ ክፍያና ለሌሎችም አጣዳፊ ተግባራት ለሚቀጥሉት ሁለት ወራት ብቻ ከፍ ያለ የገንዘብ መጠን እንደሚያስፈልግ በጥናት የተደገፈ ዝርዝር የወጪ ዘገባ ለስብሰባው ተካፋዮች ከማቅረባቸውም በላይ ይህን ገንዘብ ለማሟላት ኢዴኃኅ የኢትዮጵያውያንን ሁሉ ተሳትፎ እንደሚሻ በጥብቅ ማሳሰባቸው ተዘግቧል።

## የኢዴኃኅ የአካባቢ ውይይቶች በውጭውም ዓለም እንደሚቀጥሉ ተዘገበ።

ኢዴኃኅ እንደ አገርቤቱ ሁሉ በውጭውም ዓለም የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ አባላት በሚገኙባቸው ከተሞች ስለ ኅብረቱ የወደፊት አቀጣጫና ስለተያዙት እቅዶች በተለይም በመጪው ምርጫ የኢዴኃኅ ተግባራት ምን መሆን እንዳለባቸው የሚያብራሩ ተከታታይ ገለጻዎች ከእሁድ ጃንዋሪ 23 2005 እ. አ. አ. ጀምሮ እንደሚያካሄድ ተገለጠ።

የእሁዱ ስብሰባ በዋሽንግተን ዲሲ 16ኛው መንገድ ላይ በሚገኘው ዩኒፊኬሽን ቸርች አዳራሽ ከሰአት በሁዋላ ከቀኑ 3 00 ሰዓት ጀምሮ የሚካሄድ መሆኑ ሲታወቅ በቀጣይነት በየአስራአምስት ቀኑ በልዩ ልዩ የዓለም ከተሞች እንደሚከናወን ከአዘጋጁ ከኢዴኃኅ የሕዝብ ግንኙነትና ማስታወቂያ ቢሮ የተገኘው ዜና አብራርቷል።
ከዚሁ ጋር አዘጋጁ ኮሚቴ በቅርቡ በአገር ውስጥ የተደረጉ አበይት ክንዋኔዎችን በቪዲዮ በማስደገፍ የሚያቀርብ ሲሆን የተከታታይ ስብሰባዎቹ ዋና ዓላማ ኅብረቱ ለሕዝቡ ሕዝቡም ለኅብረቱ የሚያቀርቧቸው የወደፊት ትግል ስትራቴጂና አቀጣጫዎች የፊት ለፊት የሃሳብ መለዋወጫ መድረኮችን መፍጠር እንደሆነም ተገልጿል።

## የኢዴኃኅ አማራጭ ፕሮግራም ዝግጅት በመጠናቀቀ ላይ መሆኑና በቅርቡ ለሕዝብ ይፋ እንደሚሆን ተገለጸ።

ለ1997ቱ ምርጫ ኢዴኃኅ ለሕዝብ በአማራጭ ይዞት የሚቀርበው የኢኮኖሚ የፖለቲካና የማኅበራዊ ጉዳዮችን በጥልቀትና በስፋት የሚተነትነው አማራጭ ፕሮግራም በፌብሪዋሪ 2005 እ. አ. አ. መጨረሻ በአገር ቤትና በውጭ አገር ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ለውይይት የሚቀርብ መሆኑን ከኢዴኃኅ ቢሮ የተገኙ ምንጮች አስረዱ።
በአሁኑ ወቅት የፕሮግራሙ የመጀመሪያው ንድፍ ተጠናቆ ሁለተኛው ንድፍ በኅብረቱ የአማራጭ ፕሮግራም አርቃቂ ኮሚሽን አማካይነት የመጨረሻ መልኩን እያገኘ ሲሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለአባል ድርጅቶች ቀርቦ ግምገማ ይካሄድበትና በአገር ቤትና በውጭ አገር ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን በማቅረብ ተከታታይ ግልጽ ውይይቶችና ገለጻዎችን በሕዝባዊ ስብሰባዎች፥ በሬዲዮኖችና ጋዜጦች አማካይነት ለማድረግ ዝግጅቱ የተጠናቀቀ መሆኑ ታውቋል።

# ከኢዴኃኅ ማኅደር

## ኢዴኃኅና መሰረታዊ እምነቶቹ

በዚህ አምድ ላይ ቀደም ሲል ኅብረቱ የወሰዳቸውን አቋሞችና መተክላዊ እምነቶቹን ከማህደሮቹ እየፈተሽን እንዳሉ እናቀርባለን፡፡ ለዛሬው የመረጥነው መስራች ጉባዔው ኅብረቱን ለመመሥረት

